# የዜጎች በጀት

## የ2018 በጀት ዓመት ለዜጎች የተዘጋጀ የበጀት መረጃ ሰነድ



### በውስጥ ገፆቻችን ምን ያገኛሉ?

- **ስለ ኢትዮጵያ ማክሮ-ኢኮኖሚ ማሻሻያ፤**
- **የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ ምንድን ነዉ?**
- **በጀት ማለት ምን ማለት ነዉ?**
- **የ2018 በጀት ዓመት አጠቃላይ የበጀት ሁኔታ፤**

አጠቃላይ የማክሮ-ኢኮኖሚክ አፈጻጸምና ትንበያ፤
የ2018 በጀት ዋና ዋና የገቢ ምንጮች የትኞቹ ናቸዉ?
በበጀቱ አመቱ የሚተገበሩ ቁልፍ የታክስ ፖሊሲ ማሻሻያዎች፤
የመንግስት በጀት በምን ላይ ይዉላል?
መንግስት የገቢ በጀት ጉድለቱን እንዴት ይሸፍናል?
የ2018 በጀት አመዳደብ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ያስገባ ነዉ፤
በ2018 በጀት አመት በካፒታል በጀት ቅድሚያ የተሰጣቸዉ ወጪዎች፤
የ2018 በጀት ዓመት የክልሎች ድጎማና ዘላቂ ልማት ግቦች በጀት፤

- **የበጀትና ፋይናንስ ቴክኒካል ቃላቶችና ሓረጎች መግለጫ፤**

## 1. የዜጎች በጀት ሠነድ ምንድነዉ?

የዜጎች በጀት የመንግስት ፋይናንስ መረጃን ለሕዝብ ቀላልና በሚገባ እንዲያውቅ በቀላሉ የተዘጋጀ የብሔራዊ በጀት ስሪት ነው።በኢትዮጵያ ውስጥ በጀቱ የልማት ቅድሚያዎችን ለማስፈጸም፣አገልግሎት ለመስጠትና ድህነትን ለመቀነስዋና ሚና ስለሚጫወት፣ዜጎች የህዝብ ሀብቶች እንዴት እንደሚሰበሰቡ፣ እንዴት እንደሚመደቡና እንዴት እንደሚጠቀሙ በግልጽ ማወቃቸው አስፈላጊነው።

የበጀት መረጃን በቀላልና ያለ ቴክኒካዊ ቋንቋ በተለያዩ ሳቢ በሆኑ ምስሎችና ማጠቃለያዎች ጋር በማቀርብ የዜጎች በጀት ሰነድ ዜጎችን፣የማህበረሰብ ድርጅቶችንና ብሔራዊ እና አካባቢያዊ ሚዲያን በበጀት ሂደት በተግባር እንዲሳተፉ ያበረታታቸዋል። በመሆኑም የኢትዮጵያ የዜጎች በጀት የማህበረሰቡን ድምፅና ፍላጎቶች በብሔራዊ ቅድሚያዎች ውስጥ እንዲገልጹ እና የህዝብ ሀብት በፍትሃዊና በተመጣጣኝ ልማት እንዲዉል የሚያስችል መሳሪያነው።

| ህደቶች | የጊዜ ሠሌዳ | ዋና ዋና ተግባራት |
| --- | --- | --- |
| 1. የበጀት ዝግጅት | **የበጀት አመቱ ከመጀመሩ በፊት** | **ዕቅድ እና የስትራቴጂ አቅድ**<br>· **የአምስት ዓመት ብሔራዊ እቅድ**፡ የገንዘብ ሚኒስቴር ዋና ዋና የኢኮኖሚ ግቦችን ለማስቀመጥ የ5 ዓመት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ያዘጋጃል።<br>· **የሶስት ዓመት የክልሎች የፋይናንስ ድጋፍ**፡ በሚቀጥለው 3 ዓመት እያንዳንዱ ክልል የሚቀበለው የፋይናንስ ድጋፍ ግምት ይደረጋል።<br>· **የዓመቱ የፋይናንስ እቅድ**፡ ለአንድ ዓመት የገቢ፣ የወጪና የብድር ዝርዝር ዕቅድ ይዘጋጃል፣ ከዚያም በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ይፈቀዳል። |
| **2. በጀትን ማጸደቅ** | **የበጀት አመቱ ከመጀመሩ በፊት** | **ህጋዊነት እና የበጀት ግልጽነት**<br>· **የፓርላማ ክርክር**፡ ረቂቅ በጀት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዉይይት ተደርጎበት በመጨረሻ ይጸድቃል።<br>· **የፀደቀን በጀት ግልጽ ማድረግ**፡ የተፈቀደው የመጨረሻ በጀት በኔጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ይፋ ይደረጋል፣ ከዚያም የሕጋዊ ሰነድ ይሆናል። |
| **3. የጸደቀን በጀት ስራ ላይ ማዋል** | **በጀት አመቱ** | **ትግበራና እና ክትትል**<br>· **የስራ መርሐ ግብር**፡ የመንግስት ተቋማት የተፈቀዱላቸውን በጀቶች ተቀብለው የስራ መርሐ ግብሮቻቸውን ያዘጋጃሉ። |
| **4. የበጀት ቁጥጥርና ግምገማ** | **የበጀት አመቱ ካለቀ በኋላ** | **ቁጥጥር እና ኦዲት**<br>· **ዋናዉ ኦዲተር መስሪያ ቤት**፡ በሁሉም የህዝብ ተቋማት የፋይናንስ መለያዎችን እና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ይመረምራል፣ ይህም ገንዘቡ በትክክል |

# 3. የ2018 በጀት ዓመት አጠቃላይ የበጀት ሁኔታ

## 3.1. አጠቃላይ የማክሮ-ኢኮኖሚክ አፈጻጸምና ትንበያ

| | ዝርዝር ጉዳዮች | የ2017 በጀት አመት አፈጻጸም | የ2018 በጀት አመት ዕቅድ (ትንበያ) |
|---|---|---|---|
| | የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት | 8.40% | 8.90% |
| | የዋጋ ንረት | 13.90% | 11.90% |
| | የገቢ ዕቃዎች ወጪ | የአሜሪካን ዶላር 19.2 ቢሊዮን | የአሜሪካን ዶላር21.3 ቢሊዮን |
| | የበጀት ጉድለት | ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት የ2.06 ከመቶ | ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት የ1.0 ከመቶ |
| | የትሬዠሪ ቢል የማበደሪያ የወለድ መጣኔ በአማካይ | 16.50% | 16.38% |

የ2018 በጀት በጥንቃቄ ላይ ተመስርቶ አስደማሚ የፊስካል አፈጻጸም ሊያረጋግጥ የሚችል ከመሆኑ አንጻር በምቹ የኢንቨስትመንት አካባቢ ተጨማሪ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር እንዲሁም በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች የተፋጠና ዕድገትን ሊያስመዘግብ የሚችል ነዉ።

3.2. የ2018 በጀት ዋና ዋና የገቢ ምንጮች የትኞቹ ናቸዉ?
ከ2018 በጀት አመትየሚጠበቀው አጠቃላይ ገቢ ብር 1.93 ትሪሊዮንሲሆን፤ የገቢ ምንጩ በዋነኝነት ከሀገር ውስጥ ገቢዎች በታክስማሰባሰብ እንዲሁምከሌሎች የሀገር ውስጥ ምንጮችማለትም የውስጥ ብድር፣ከውጭ ልማት ድገፍእና የውጭ ብድርን የሚጨምር ነዉ።




Revenue Sources for EFY 2018 (2025/26) Budget/In Billion

# በበጀቱ አመቱ የሚተገበሩ ቁልፍ የታክስ ፖሊሲ ማሻሻያዎች፤




## ሀ. የታክስ ገቢዎች

- የዝቅተኛ አማራጭ ገቢ ግብር፤
- የቅድሚያ ግብር መጣኔ፤
- የአክሳይዝ ታክስን ማስተዳደር:- ዘመናዊ የቴምብር ሥርዓት ለመዘርጋት የተጀመረው ሥራ ተጠናቆ በበጀት አመቱ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ የሚደረግ፤
- በነዳጅ ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ (15%) ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚ እንደሚሆን ይጠበቃል።
- በነዳጅ ላይ የተጣለውን የተቸማሪ እሴት ታክስ ምጣኔ (15%) ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ለማድረግ ዕቅድ ተይዟል።
- አዲሱ የንብረት ታክስ አዋጅ በየክልሉ በተመረጡ ከተሞች በክልሎች በኩል ህጎችን በማጽደቅ ተፈጻሚ የሚደረግ ይሆናል።
- በነዳጅ በሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚጣል የሞተር ተሽካርካሪ ሥርጭት ታክስ በህግ ለመጣል ዕቅድ ተይዟል።

## ለ. ታክስ ያልሆኑገቢዎች

- የውጭ ሀብት አሰባሰብን ለማሻሻል ከልማት አጋሮች ጋር ስትራቴጂካዊ በሆነ መንገድ ግንኙነቶችን ለማሻሻል ይሰራል፤
- ከልማት አጋሮች በበጀት ድጋፍ መልክ የሚገኙ የውጭ ሀብቶች ለበጀት መሸፈኛ በገቢ በጀት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል።
- ከፕሮጀክቶች ዕርዳታና ብድር የሚገኙት ገቢዎች በቀጥታ ለፕሮጀክቶቹ ማስፈጸሚያ ብቻ ይዉላሉ፤
- በአንጻሩ ወደ ትሬዠሪ በቀጥታ የሚፈሱት የብድርና ዕርዳታ ገቢዎች በልማት አጋሮችእና በመንግስት በተደረሱ ስምምነቶች መሠረት ይሆናሉ፤

## 3.3. የመንግስት በጀት ለምን ላይ ይዉላል?

ለ2018 በጀት አመት አጠቃላይ ብር 1.93 ትሪሊዮን የተመደበ ሲሆን፤ በባለፈዉ በጀት አመት ከተመደበዉ የብር 493.5 ብልጫ ወይንም የ34.4 በመቶ አሳይቷል። የበጀት አመዳደቡም እንደሚከተለዉ ቀርበዋል።

WWW.MOFED.GOV.ET



# የ2018 በጀት አመዳደብ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ያስገባ ነዉ፤

**The EFY 2018 (2025/26) program budget was prepared with the following key considerations:**

### 1.በረጅም ጊዜ ከተተለሙ የልማት ዕቅዶች ጋር ያለዉ ቁርኝት

- በአስር አመቱ የልማት ዕቅድ ስር ከ2016 እስከ 2018 በጀት አመት የተተለመዉ የልማትና የኢንቨስትምነት ዕቅድ፤
- በፕሮግራም በጀት በተቀመጡ ግቦች እና በሚመነጭ የሀብት መጠን፤

### 2. የማክሮ-ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች.

- ከተደረጉ ሪፎርሞቹ ጋር ለማመጣጠን በገበያ የሚወሰን የዉጪ ምንዛሪ፣ የደመዋዝ ማስተካከያና የታሪፍ ለዉጦች መሰረት ማስተካከያዎችን ማድረግ፤

### 3. የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሽግግሮች ቅድመ-ሁኔታዎች

- የኢንዱስትሪ ልማትና የወጪ ንግድ ማስፋት፤
- ስራ ፈጠራ፣ የግብርና ስራ ዉጤታማነት እና መስኖ ልማት ዕድገት፤

### 4. የካፒታል ፕሮጀክቶች

- ለነባር ፕሮጀክቶች ቅድሚያ መስጠት፤
- በዉጪ ፋይናንስ በሚደረጉ ፕሮጀክቶች ከመንግስት የሚጠበቅ የበጀት ድርሻ፤

### 5. ሀገራዊ ደህንናትና ማህበራዊ ዋስትና

- ለሀገር ደህንነት ማስጠበቂያ የሚደረግ ወጪ፤
- በተፈጥሮና በሰዉ ሠረሽ አደጋ ለተጠቁ ወገኖች የሚደረግ ድጋፍ፤
- ለልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም፤

### 6. በደህረ ጦርነት ለመልሶ ማቋቋሚያ

- በጦርነቱ የተጎዱ መሰረተ-ልማቶችንና አገልግሎቶችን ወደ ቀድሞ አቋማቸዉ መመለስ፤

### 7. የዕዳክፍያ

- ለሀገር ዉስጥና ለዉጭ ሀገር ዕዳ የሚደረግ የዕዳ ክፍያ ግዴታ፤

### 8. ለዘላቂ ልማት ግቦች

- የዘላቂ ልማት ግቦች ተፈጻሚ ለማድረግ ያለዉ ከፍተኛ ፍላጎት፤
- ለአነስተኛና መካከለኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከመንግስት የሚጠበቅ የወጪ ድርሻ፤
- ጅምር የመስኖ ልማት ስራዎችን ማጠናቀቅ፤

### 9.በዉጤት ላይ የተመሰረቱ ዕቅዶች

- ከልማትና መሰረታዊ አገልግሎት አቅርቦት አንጻር ከመንግስት ተቋማት የሚቀርቡ በተጨባጭ ዉጤት የሚያመጡና በዘላቂነት ችግር የሚፈቱ ዕቅዶች ላይ ትኩረት ይደረጋል፤

## 3.4. መንግስት የገቢ በጀት ጉድለቱን እንዴት ይሸፍናል?






## የ2018 በጀት ዓመት የክልሎች ድጎማና ዘላቂ ልማት ግቦች በጀት ድርሻ፤/በቢሊዮን ብር/

| የክልሎች ዝርዝር | የክልሎች ድጋፍ | ለዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|
| **ድምር** | **314,756,994,045** | **14,000,000,000** | **328,756,994,045** |
| **ለትግራይ ክልል** | 18,979,846,741 | 844,200,000 | **19,824,046,741** |
| **ለአፋር ክልል** | 9,505,661,220 | 422,800,000 | **9,928,461,220** |
| **ለአማራ ክልል** | 67,987,510,714 | 3,024,000,000 | **71,011,510,714** |
| **ለኦሮሚያ ክልል** | 108,465,260,148 | 4,824,400,000 | **113,289,660,148** |
| **ለሱማሌ ክልል** | 31,412,748,005 | 1,397,200,000 | **32,809,948,005** |
| **ለቤንሻንጉል/ጉሙዝ ክልል** | 5,760,052,991 | 256,200,000 | **6,016,252,991** |
| **ለጋምቤላ ሕዝቦች ክልል** | 4,186,268,021 | 186,200,000 | **4,372,468,021** |
| **ለሐረሪ ሕዝብ ክልል** | 2,392,153,155 | 106,400,000 | **2,498,553,155** |
| **ለድሬዳዋ አስተዳደር** | 2,769,861,548 | 123,200,000 | **2,893,061,548** |
| **ለሲዳማ ክልል** | 12,912,716,827 | 574,341,600 | **13,487,058,427** |
| **ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል** | 9,774,673,447 | 434,765,330 | **10,209,438,777** |
| **ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል** | 22,026,994,841 | 979,733,361 | **23,006,728,202** |
| **ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል** | 18,583,246,387 | 826,559,709 | **19,409,806,096** |

# የበጀትና ፋይናንስ ቴክኒካል ቃላቶችና ሓረጎች መግለጫ፤

**1)የአስተዳደር ስልጣን:-**በመንግስት አስተዳደር ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ ያለው የስልጣን ተዋረድ ማለት ነዉ።

**2)የበጀት ጉድለት፡-** በበጀት ዓመቱ በወጪና ገቢ በጀት መካከል ያለ ልዩነት ሲሆን፤ መጠኑም ከጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት አንጻር በመቶኛ የሚቀመጥ ነዉ።

**3)የበጀት ድጋፍ፡-** የፌዴራሉ መንግስት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን ዓመታዊ የበጀት ድጋፍ ነው።

**4)የካፒታልወጪ፡-**በተቋማት የመንግሰትን አገልግሎት ለመስጠትና ለማሻሻል ቋሚ ሀብት ለማፍራት ወይንም ለማሻሻል የሚዉል ወጪ ነዉ።

**5)የንብረትግብር:** በከተማ ዉስጥ በሚገኝ በርግጥ ንብረት ላይ የሚጣል የንብረት ግብር ሲሆን፤ ግብር ከፋይ እንዲከፍል የሚጣል ግብር ነዉ።

**6) የዜጎች በጀት፡-** መሠረታዊ የበጀት መረጃዎች ዜጎች ሊረዱት በሚችሉ ቀላል እና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ተደራሽ የሚደረግ የበጀት መረጃ ሰነድ ነው።

7) **የዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ፡-** ከመንግስት የሚሰጡ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ለማሻሻል ዜጎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድበእቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና የአፈፃፀም ግምገማ ላይ የሚያደርጉትን ሁለንተናዊ ተሳትፎን ያመለክታል።

8) **የሀገር ውስጥ በጀት ምንጭ፡-** መንግስት የበጀት ዓመቱን ወጪ ለመሸፈን ከሀገር ዉስጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚሰበስበዉ እንዲሁም ከሀገር ዉስጥ የሚያገኘዉን ብድር የሚያመለክትነዉ።

9) **የውጭ እርዳታ፡-** በመንግስት አቅም ሊሸፈኑ የማይችሉትን መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለመደገፍና ለማገዝ ከሚፈልጉ የዉጭ መንግስታትና እርዳታ ድርጅቶች የሚገኝ ሀብትን ያጠቃልላል።

10) የኢትዮጵያ በጀት ዓመት፡- በኢትዮጲያ ዘመን አቆጣጠር መሰረት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ድረስ ያለዉ አመታዊ የበጀት ትግበራ ጊዜ ማለት ነው።

11) የውጭ ብድር፡- **መንግስት የወጪ ግዴታዉን ለመወጣትየሚያስፈልገዉን ሀብት ከሀገር ዉስጥ ከሚገኝ የበጀት ምንጭ መሸፈን በማይችልበት ሁኔታ የበጀት ጉድለቱን ለማሟላት ከዉጭ አበዳሪዎች የሚገኘዉን ሀብት ነዉ።**

12) **የፊስካል ፖሊሲ፡-** መንግስት ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር የመንግስት ገቢ አሰባሰብና ወጪ አደረራረግ የሚመራበት ስርዓት ነው።

13) **የፋይናንስ ሀብት/ገቢ፡-** መንግስት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚዉሉ ወጪዎችን ለመሸፈን ከታክስ፣ ታክስ ካልሆኑና ከሌሎች የገቢ ምንጮች የሚገኘዉ ገንዘብ ማለት ነው።

**14) የመካከለኛ ጊዜ የወጪ ማዕቀፍ፡-** የኢትዮጵያ መንግስት የሦስት ዓመት የወጪ ዕቅዶችን ያወጣል፡ በጀቶች የመንግስትን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የሚያንፀባርቁ እና ለመንግስት መልሶ ግንባታ እና ልማት ግዴታዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ያለመ ነው።

# የበጀትና ፋይናንስ ቴክኒካል ቃላቶችና ሓረጎች መግለጫ፤

**15) ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት፡-** በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ በአንድ ሀገር ውስጥ የተደረጉ ከሁሉም ከተጠናቀቁ ምርትና አገልግሎቶች የተገኘ የገንዘብ ዋጋ ነው።

**16) የዋጋ ግሽበት/ንረት መጠን፡-** አሁን ያለዉን የሸቀጦትና አገልግሎቶች ዋጋ ከዚህ በፊት ከነበረው ዋጋ ጋር በማነጻጸር የዋጋ ለውጡን በመቶኛ መስቀመጥ ነዉ።

**17) ማክሮ ኢኮኖሚ፡-** የአጠቃላይ ወይም ጥቅል ሀገራዊ ኢኮኖሚዉ አወቃቀር፣ አፈፃፀም፣ ባህሪንና የውሳኔ አሰጣጡን የሚያመለክት ነው።

**18) የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ፡-** አመታዊ የፊዝካል ዕቅዶችና ግቦች የፖሊሲ ትግበራ አማራጮች የሚወሰኑበት እንዲሁም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የበጀት ዓመቱ የገቢና ወጪ ግምት የሚከናወንበት ማዕቀፍ ነዉ።

**19) ሞኒተሪ ፖሊሲ፡-** አጠቃላይ የገንዘብ አቅርቦትን በመቆጣጠር ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲኖር ለማድረግ የሀገሪቱ ብሄራዊ ባንክ የሚያወጣዉና የሚተገብረዉ ስርዓት ነው።

**20) ፖሊሲ፡-** በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውና ሊተገሩ የታቀዱ ውጥኖች ማስፈፀሚያ መመሪያ ነው።

**21) ቅድመ-በጀት ውይይት፡-** በወረዳ ደረጃ የዜጎችን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ቅድመ-ፍላጎቶችና ምርጫዎች በዕቀድ ለማካተትና ለማከናወን ከወረዳዉ ማህበረሰብ ክፍሎች ጋር የሚደረግ ዉይይት ነዉ።

**22) የመንግስት ተቋማት (የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች)፡-** ማንኛዉንም የፌዴራል መ/ቤት በአዋጅ የተቋቋመና ሙሉ በሙሉም ይሁን በከፊል ከመንግስት በሚመደብላቸው በጀት የሚተዳደሩና የፋይናንስ እንቅስቃሴያቸዉ በመንግስት ቁጥጥር የሚደረግባቸዉን ያካትታል።

**23) መደበኛ በጀት (የስራ ማስኬጃ ወጪ)፡-** ቋሚ ንብረቶችን ለመፍጠር የማይዉልና መንግስታዊ ስራዎች ለማከናወን ለሚያስፈልጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ብቻ የሚያስፈልግ ወጪ ነዉ።

**24) ተንከባላይ ወጪ፡-** ከአንዱ በጀት ዓመት ወደሚቀጥለዉ የሚከባለልና በየጊዜዉ የሚተደስ ወጪን ያመለክታል።

**25) ዘላቂ የልማት ግቦች፡-** ለሁሉም የተሻለ እና ቀጣይነት ያለው ምቹ ሁኔታን ለመፍጠርና ዓለም አቀፍ ተግዳሮቶች ማለትም ድህነትን፣ ኢ-ፍትሃዊነትን፣ የአየር ንብረት ለውጥንና የአካባቢ መበላሸትን ለመቅረፍ እንዲሁምሰላምን ለማስፈን የተወጠኑ ግቦች ናቸዉ።

**ለበለጠ መረጃ፡-**

www.mofed.gov.et

infopr@mofed.gov.et

Phone: + 251-111-552-015

Addis Ababa, Ethiopia